# በብርሃን ትመላለሳህ?

## 1ዮሐ፡ መጽሐፍ ጥናት

በጃኪ አንደርሰን (Jackie Anderson) ተጽፎ
በጳውሎስ ኮይቴ የተተረጎመ

## ***መውጫ***

## ***የመሪው መመሪያ***

| | |
|---|---|
| ትምህርት 1 | 1ዮሐ፡1 |
| ትምህርት 2 | 1ዮሐ፡1፡5-10 |
| ትምህርት 3 | 1ዮሐ፡2፡1-11 |
| ትምህርት 4 | 1ዮሐ፡2፡9-11 |
| ትምህርት 5 | 1ዮሐ፡2፡15-17 |
| ትምህርት 6 | 1ዮሐ፡2፡18-19 |
| ትምህርት 7 | 1ዮሐ፡3፡1-12 |
| ትምህርት 8 | 1ዮሐ፡3፡13-24 |
| ትምህርት 9 | 1ዮሐ፡4፡1-6 |
| ትምህርት 10 | 1ዮሐ፡4፡7-21 |
| ትምህርት 11 | 1ዮሐ፡5፡1-13 |
| ትምህርት 12 | 1ዮሐ፡5፡13-21 |
| ትምህርት 13 | መዝ፡51 |

## ***ምንጭ***

መጽሐፍ ቅዱስ፡-አዲሱ መደበኛ ትርጉም
እግዚአብሔር አባትህን እንዴት ታውቃለህ? በ Kay Arthur እና David Lawson የተጻፈ
አዲሱ የመጽሐፍ ቅዱስ አጠናን ዘዴ፡ በ Thomas Nelson Publisher's የተጻፈ
የእግዚአብሔርን ቃል መረዳት፡ በ J. Scott Duval እና J. Daniel Hays የተጻፈ

## <u>ትምርት 1</u>

**<u>በብርሃን ትመላለሳለህ? (1ዮሐ፡1)</u>**

***<u>መግቢያ፡-</u>*** መሪው ድምጹን ከፍ አድርጎ ያነባል፡- ብዙ ሰዎች ወደ ቤተክርስቲያን ይሄዳሉ፡፡ በኳየር ይዘምራሉ፤ ለቤተክርስቲያን ሕግም ይታዘዛሉ፡፡ ነገር ግን ሙሉ በሙሉ ክርስቲያን ናቸው ማለት ይከብዳል፡፡ ብዙዎቹ ወደ መንግሥተ ሰማይ ለመግባት ተስፋ ያደርጋሉ፡፡ ግን ለመግባታቸው እርግጠኛ አይደሉም፡፡ ምናልባት ከእግዚአብሔር ጋር ላለህ ግንኙነት አንተ ወይም ሌላ ሰው ልጠራጠር ይችላል፡፡ እግዚአብሔር አባታችን እንደሆነ እንድናውቅ መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስተምረንን እውነት ምን እንደሆነ ዛሬ መማር እንጀምራለን፡፡

ደግሞ መጽሐፍ ቅዱስን እንዴት ማጥናት እንሚቻል እንማራለን፡፡ መጽሐፍ ቅዱስን ለማጥናት ሦስት ክፍሎች አሉ፡-

1. ምልከታ (የመጽሐፉን ክፍል ጠቅለል አድርጎ መመልከት)----- የምዕራፉ አጠቃላይ አሳብ ምንድነው?
2. ትርጉም---- የምዕራፉ ትርጉም ምንድነው?
3. ከሕይወት ጋር ማዛመድ---- ክፍሉ ለሕይወቴ ምን ያስተምረኛል?

ጊዜ ወስደህ ክፍሉን ደጋግመህ አንብብ፡፡ የመጽሐፉ ክፍል ምን እንደሚል በጥንቃቄ ተመልከት፡፡ ከዚያ በኋላ የበለጠውን የክፍሉን ትርጉም ለማግኘትና ከሕይወት ጋር ለማዛመድ ትችላለህ፡፡

**<u>ምልከታ(የመጽሐፉን ክፍል ጠቅለል አድርጎ መመልከት)</u>**

***<u>ለመሪው፡-</u>*** አንድ ሰው 1ዮሐ፡1-4፣ 2፡1-2 ቁ፣26፣5፡13 ድምጹን ከፍ አድርጎ እንዲያነብ አድርግ፡፡

**<u>የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች</u>**

1ዮሐ፡1፡1-4፡-

ስለ ሕይወት ቃል ከመጀመሪያው የነበረውንና የሰማነውን በዓይኖቻችንም ያየነውን የተመለከትነውንም እጆቻችንም የዳሰሱትን እናወራለን፤
ሕይወትም ተገለጠ አይተንማል እንመሰክርማለን፣ ከአብ ዘንድ የነበረውንም ለእኛም የተገለጠውን የዘላለምን ሕይወት እናወራላችኋለን፤
እናንተ ደግሞ ከእኛ ጋር ሕብረት እንዲኖራችሁ ያየነውንና የሰማነውን ለእናንተ ደግሞ እናወራላችኋለን፡፡ ሕብረታችንም ከአባት ጋር ከልጁም ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ነው፡፡ ደስታችሁም እንዲፈጸም ይህን እንጽፍላችኋለን፡፡

1ዮሐ፡2፡1-2፡-

ልጆቼ ሆይ ሐጢአትን እንዳታደርጉ ይህን እጽፍላችኋለሁ፡፡ ማንም ሐጢአትን ቢያደርግ ከአብ ዘንድ ጠበቃ አለን እርሱም ጻድቅ የሆነ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ እርሱም የሐጢአታችን ማስተስሪያ ነው፤ ለሐጢአታችንም ብቻ አይደለም፤ ነገር ግን ለዓለሙ ሁሉ ሐጢአት እንጂ፡፡

1ዮሐ፡2፡26፡-

ስለሚያስቱአችሁ ሰዎች ይህን ጽፌላችኋለሁ፡፡

1ዮሐ፡5፡13፡-

የዘላለም ሕይወት እንዳላችሁ ታውቁ ዘንድ በእግዚአብሔር ልጅ ስም ለምታምኑ ይህን ጽፌላችኋለሁ፡፡
አሁንም አንድ ሰው ለሁለተኛ ጊዜ ድምጹን ከፍ አድርጎ ያነባል፡፡ በዚህ ጊዜ እያንዳንዳችሁ ‹‹እጽፍላችኋለሁ፤ጻፍሁላችሁ› የሚሉ ቃላቶችን ከላይ በተጠቀሱ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ከሥር አስምሩባቸው፡፡

***መሪው የሚከተለውን ሀሳብ ከፍ አድርጎ ያነባል፡-*** 1ዮሐ፡ መጽሐፍ ከኢየሱስ ሐዋሪያቶች በአንዱ እንደተጻፈ ታሪክ ይናገራል፡፡ መጽሐፉን በትክክል ለመተርጎም ከሁሉ ነገር በቅድሚያ የመጽሐፉን ዓላማ ማወቅ ጠቃሚ ነው፡፡ ለዚህ ከፍል ሌሎች ጥያቄዎች ሊኖሩአችሁ ይችላሉ፡፡ ነገር በቅድሚያ ሐዋሪያው ዮሐንስ መልእክቱን ለምን እንደጻፈ ትኩረት ማድረግ አለብን፡፡

በመጀመሪያ እነዚህን ክፍሎች በጥንቃቄ ተመልከት፤ ዮሐንስ ለምን እንደጻፈ ይነግራችኋል፡-

1. ሐዋሪያው ዮሐንስ ይህንን መልእክት ለምን ጻፈ? አራቱን ምክንያቶች ግለጽ፡፡ የዮሐንስን መልእክት ጠቅለል አድርገን ስንማር እያንዳንዱን ምክንያት እናገኛለን፡፡
2. ዮሐንስ የሚያውጀው ምንድነው? የዚህ አዋጅ ውጤቱ ምንድነው?
3. የዮሐንስን ደስታ ፍጹም የሚያደርገው ምንድው?
4. እናንተ ምን እንድታውቁ ነው ዮሐንስ የሚፈልገው?

ጥቂት ሰዎች ብቻ ወደ መንግሥተ ሰማይ ለመግባት ተስፋ ያደርጋሉ፡፡ ነገር ግን በውስጣቸው ይጠራጠራሉ፡፡ በ1ዮሐ፡5፡13 ዮሐንስ የሚናገረው ይህንን ነው?
1ዮሐ፡5፡13 ላይ ያለውን ጥቅስ ከዚህ በታች ባለው ቦታ ጻፍና በቃል አጥና፡-

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

***ለመሪው***፡- 1ዮሐ፡1፡1-3 እንደገና አንብብ፡፡ በዚህ ጊዜ የዮሐንስን ስም በሚጠቅሰው በእያንዳንዱ ቃል ላይ ምልክት አድርግበት፡፡ (ለምሳሌ፡- ‹‹እና------አለን›› የሚለው ቅድመ ቅጥያና መድረሻ ቅጥያ ያለባቸው ቃላቶች (ለምሳሌ፡ ‹‹እና--ወራ---ለን››) የሚሉና ‹‹እኛ፤ለእኛ›› የሚሉ ቃላቶች ስለ ዮሐንስ ያወራሉ፡፡ በእነዚህ ቃላቶች ላይ የክብ ምልክት በማድረግ ከሌሎች ልትለያቸው ትችላለህ፡፡ ደግሞ የየኢየሱስን ስም በሚጠቅሱ ቃላቶች ላይ የመስቀል ምልክት ልታደርግ ትችላለህ፡፡

የትርጉምና የውይይት ሀሳቦች

1. ስለ ዮሐንስ ምን እንማራለን? በእነዚህ ጥቅሶች መሠረት ዮሐንስ የዳሰሰው፤የሰማውና ያየው ማንን ነበር?
2. ሐዋሪያው ዮሐንስ ‹‹እኛ፤የእኛ፤እኛን›› የሚሉ የብዙ ቁጥር መገለጫ ቃላቶችን ይጠቀማል፡፡ እነዚህ ብዙ ቁጥር መገለጫዎች ሐዋሪያትን እንደሚያመለክቱ የመጽሐፍ ቅዱስ ተርጓሚዎች ይናገራሉ፡፡
3. ስለ ኢየሱስ ምን እንማራለን? ኢየሱስን የሚገልጹ ቃላቶችን ዘርዝር፡፡ ለምሳሌ፡- ‹‹የሕይወት ቃል›› የሚለው እሱን ከሚገልጹ ቃላቶች አንዱ ነው፡፡
4. ዮሐንስ ከጌታ ጋር ባደረገው ልምምድ ላይ ትኩረት የሚያደርገው ለምንድነው?

ከሕይወት ጋር ማዛመድ

1. ዛሬ የተማርካቸው የመጽሐፍ ቅዱስ አጠናን ዘዴዎች ምንድናቸው?
2. ከእሱ ጋር ያለህን ግንኙነት እንድታውቅ ጌታ ዛሬ ከአንተ የሚፈልገው ምንድነው?
3. የዘላለም ሕይወት እንዳለህ ታውቃለህ?

## ትምህርት 2
## በብርሃን ትመላለሳለህ (1ዮሐ፡1፡5-10)

### ምልከታ (መመልከት)

**ለመሪው፡-** እስቲ የመጽሐፍ ቅዱስ አጠናን ዘዴዎችን እንደገና እንከልሳቸው፡፡ ማን ያስታውሳል?

**መግቢያውን ከፍ አድርገህ አንብብ፡-** ባለፈው ሳምንት ሐዋሪያው ዮሐንስ ይህንን መጽሐፍ የጻፈበትን ምክንያት ተምረን ነበር፡፡ እነዚህ ምክንያቶች ምን ነበሩ? ከዚህ ክፍል የተነሣ ባለፈው ሳምንት በሕይወቱ ለውጥ የመጣለት ሰው ካለ ሊያካፍለን ይችላል? በዚህ ሳምንት ስለ እግዚአብሔርና ስለ መጽሐፍ ቅዱስ የበለጠውን እንማራለን፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ ጥንቃቄ የተሞላበት ምልከታ እናደርጋለን፡፡

**1ዮሐ፡1፡5-10፡- *መሪው ድምጹን ከፍ አድርጎ ያነባል፡፡***

ቁ፡5 ከእርሱም የሰማናት ለእናንተም የምናወራላችሁ መልእክት፡- እግዚአብሔር ብርሃን ነው ጨለማማ በእርሱ ዘንደ ከቶ የለም የምትል ይህች ናት፡፡
ቁ፡6 ከእርሱ ጋር ሕብረት አለን ብንል በጨላማም ብንመላለስ እንዋሻለን እውነትንም አናደርግም፤
ቁ፡7 ነገር ግን እርሱ በብርሃን እንዳለ በብርሃን ብንመላለስ ለእያንዳንዳችን ሕብረት አለን፤የልጁም የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከሐጢአት ሁሉ ያነጻናል፡፡
ቁ፡8 ሐጢአት የለብንም ብንል ራሳችንን እናስታለን፤እውነትም በእኛ ውስጥ የለም፡፡
ቁ፡9 በሐጢአታችን ብንናዘዝ ሐጢአታችንን ይቅር ሊለን ከዓመፃም ሁሉ ሊያነጻን የታመነና ጻድቅ ነው፡፡
ቁ፡10 ሐጢአትን አላደረግንም ብንል ሐሰተኛ እናደረገዋለን ቃሉም በእኛ ውስጥ የለም፡፡

መጽሐፍ ቅዱስን ስናነብ ማድረግ ያለብን አንዱ ነገር የሚቃረኑ ሃሳቦችን መፈለግ ነው፡፡ በዚህ ሥፍራ ዋናው የሚቃረነው ሀሳብ ብርሃንና ጨለማ ነው፡፡ የእግዚአብሔር ባሕሪ ከጨለማ ጋር ይቃረናል፡፡
ሌላው የሚቃረነው ሀሳብ የእኛ ምልልስ ነው፡፡ የሚከተለውን ሠንጠረዥ (ቻርት) ሙላ፡፡ የመጀመሪያው ምሳሌ ተሠርቶልሃል፡፡ ምናልባት ይህ የሚከብድ ከሆነ ክፍሉን መልሰህ መላልሰው ማንበብ እንዳለብህ አትዘንጋ፤እግዚአብሔር እንዲረዳህ ፀልይ፡፡

| **በብርሃን መመላለስ** | **በጨለማ መመላለስ** |
| --- | --- |
| 1. እርስ በርስ ሕብረት ማድረግ | 1. ከእግ/ር ጋር ሕብረት ሳይሆኖረን አለን ካልን |
| 2. | 2. |
| 3. | 3. |
| 4. | 4. |
| 5. | 5. |
| 6. | 6. |
| 7. | 7. |

## የትርጉምና የውይይት ሀሳቦች

1. ከዚህ ሠንጠረዥ ምን ትማራለህ?
2. ሠንጠረዡን ተመልከትና ስለ ጨለማ ያለህን ሀሳብ ተወያይ
3. በዚህ ሠንጠረዥ ውስጥ እንደ ሀሰተኛ ትምህርት የተወሰደው የትኛው ነው
4. ስለ እግዚአብሔር ምን ትማራለህ?
5. 1ዮሐ፡1፡7 እንደገና አንብብ፡፡ እኛ በብርሃን የምንመላለስ ከሆነ ሊሆኑ የሚችሉ ሁለት ነገሮች ምንድናቸው?

1________________________2__________________________________፡፡

6. ‹‹ሕብረት ማድረግ›› የሚለውን ሐረግ ፈልግ፡፡ ይህ ሐረግ ስንት ጊዜ ነው የተደጋገመው? ይህ ቁልፍ ቃል ነው፡፡ በአንድ ሃሳብ ላይ ያለው ቁልፍ ቃል የክፍሉን ትርጉም እንድናውቅ ይረዳናል፡፡ የክርስቲያን ሕብረት ማለት ምን ማለት ነው? ይህ ‹ሕብረት› የሚለው ቃል ከሁለት ሃሳብ የመነጨ ነው፡፡ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ሰዎች በአንድ ላይ በመርከብ መሄድ ማለት ነው፡፡ ይህን ‹ሕብረት› የሚለውን ቃል የያዙትን ቁጥሮች እንደገና ተመልከት፡፡ ከዚህ ምን እንማራለን?

7. አንድ ሰው ሐጢአትን ቢያደርግ ከእግዚአብሔር ጋር ያለውን ግንኙነት እንዴት ሊጎዳ ይችላል?
8. ይህ ማለት በብርሃን ከሚመላለስ ሰው ጋር <u>ሕብረት</u> ማድረግ አንችልም ማለት ነው?
9. ሌላው የተደጋገው ቃል ሐጢአት ነው፡፡ በቁ.5-10 ባለው ክፍል ውስጥ ይህንን ሀሳብ ተመልከት፡፡ ስለ ሐጢአት ምን ትማራለህ? ለሐጢአት ተጨማሪ ትርጉም እንድንሰጥ የሚረዱን ሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች የትኞቹ ናቸው?

## የትርጉምና የውይይት ሀሳቦች

ሐዋሪያው ዮሐንስ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረን ሐጢአት መሥራት እንደሌለብን ይጽፍልናል፡፡ ስለ እነዚህ ጥቅሶች ስትወያይ የዚህን መጽሐፍ ዓላማ አስታውስ፡፡ ወደ ፊት ጠለቅ ብለን ስንገባ ስለ እነዚህ ሀሳቦች የበለጠውን እንማራለን፡፡
በብርሃን ወይም በጨለማ መመላለስ የሚለው በየዕለቱ የምንኖረውን አኗኗር ያሳያል፡፡ ክርስቲያን ነኝ እያለ ግን በጨለማ የሚመላለስ ሰው ታውቃለህ? እንዲህ ዓይነቱን ሰው ሐዋሪያው ዮሐንስ ምን ይላል? አንድ ሕፃን መራመድ ስለሚፈልግ ከጥቅት ጊዜ በኋላ

መራመድን ይማራል። እንዲሁም አንድ አዲስ ክርስቲያን በብርሃን መመላለስ ስለሚፈልግ እግዚአብሔር እጁን ስለ ያዘ በብርሃን ይመላለሳል።

## ከሕይወት ጋር ማዛመድ

1. ዛሬ የተማርነው የመጽሐፍ ቅዱስ አጠናን ዘዴ ምንድነው?
2. እግዚአብሔር አባታችን ነው ካልን እንዴት መመላለስ አለብን? ለምን?
3. ዛሬ ማታ ወደ ቤት ስትሄድ ‹‹እኔ በብርሃን አመላለሳለሁ ወይስ በጨለማ?›› ብለህ ራስህን ጠይቅ። በብርሃን መመላለስ አለመመላለስህን በምን ታውቃለህ?

# ትምህርት 3

**በብርሃን ትመላለሳለህ? (1ዮሐ፡2፡1-6)**
**ለመሪው፡- የሚከተሉትን ጥያቄዎችን ለቡድንህ አቅርብ።**
መጽሐፍ ቅዱስን በሚገባ ለማጥናት የሚረዱ ሦስቱ ዘዴዎች ምንድናቸው?
ከባለፈው ሳምንት ትምህርት የምታስታውሳቸው የአጠናን ዘዴዎች ምንድናቸው?
ሐዋሪያው ዮሐንስ ይህንን መልዕክት ለምን ጻፈ?

**አሁን ድምጽህን ከፍ አድርገህ የሚከተለውን አንብብ፡-** እግዚአብሔር ብርሃን እንደሆነ ባለፈው ሳምንት ተምረን ነበር። በእሱ ጨለማ የለም። በጨለማ እየተመላለስን ከእግዚአብሔር ጋር ሕብረት አለን ማለት አንችልም። ከእግዚአብሔር ጋር ያለን ግንኙነት የሚታወቀው በብርሃን ስንመላለስ ብቻ ነው። በብርሃን ስንመላለስ ምን ይሆናል? እግዚአብሔር ከሐጢአት ሁሉ ያነጻናል። ሁል ጊዜ ሐጠአተኞች መሆናችንን ማመንና ሁል ጊዜ ከእግዚአብሔር ይቅርታን መለመን አለብን።

**ምልከታ፡-**

1ዮሐ፡2፡1-6 ድምጽህን ከፍ አድርገህ አንብብ፡-
ቁ፡1 ልጆቼ ሆይ ሐጢአትን እንዳታደርጉ ይህን እጽፍላችኋለሁ። ማንም ሐጢአትን ቢያደርግ ከአብ ዘንድ ጠበቃ አለን እርሱም ጻድቅ የሆነ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።
ቁ፡2 እርሱም የሐጢአታችን ማስተስሪያ ነው፤ ለሐጢአታችንም ብቻ አይደለም፤ ነገር ግን ለዓለሙ ሁሉ ሐጢአት እንጂ።
ቁ፡3 ትዕዛዛቱንም ብንጠብቅ በዚህ እንዳወቅነው እናውቃለን።
ቁ፡4 አውቄዋለሁ የሚል ትዕዛዛቱንም የማይጠብቅ ውሸተኛ ነው እውነትም በእርሱ ውስጥ የለም።
ቁ፡5 ቃሉን ግን የሚጠብቅ ሁሉ በእርሱ የእግዚአብሔር ፍቅር በእውነት ተፈጽሞአል። በእርሱ እንዳለን በዚህ እናውቃለን።
ቁ፡6 በእርሱ እኖራለሁ የሚል እርሱ እንደ ተመላለሰ ራሱ ደግሞ ሊመላለስ ይገባዋል።

ይህን ክፍል እንደገና ድምጽህን ከፍ አድርገህ አንብብ። ከዚያም የኢየሱስን ስም በሚጠሩና ስለእርሱ በሚያወሩ ቃላቶች በላያቸው የመስቀል ምልክት አድርግ።

‹ሐጢአት› የሚለው ቃል የት ቦታ እንደተገለጸና እንዲሁም ‹እናውቃለን› የሚለው ቃል የት ቦታ እንደተገለጸ አግኝ፡፡

**የትርጉምና የውይይት ሀሳቦች**

1. ዮሐንስ ይህንን መልዕክት ለምን ጻፈ?
   ቁ.1________________________________
2. ሐጢአትን ፈጽሞ አለማድረግ ይቻላል?
3. እውነተኛ ሕይወታችን እኛ ደካማ እንደሆንና ሐጢአት ላይ እንደምንወድቅ ይነግረናል፡፡ ስለዚህ ዮሐንስ እዚጋ በቁ.1 የሚለው ምንድነው?
4. በሐጢአት ላይ ያለን አመለካከት ከዚህ በታች ቀርቧል፡፡ ከራስህ ሕይወት ምሳሌ በመስጠት ተወያይ፡፡
   - 4.1. ‹‹ሐጢአት ሠርቻለሁ›› ብሎ መናገር ይከብዳል፡፡ ወይ የሠራኸውን ሐጢአት ትደብቀዋለህ፣ወይ ግድ የለም ትላለህ፣ወይም ለመከላከል ትፈልጋለህ፡፡
   - 4.2. በሐጢአት ምክንያት የሚመጣውን አደጋ ትክዳለህ፡፡ ሐጢአቴ ይቅር ስለተባለለኝ ግድ የለኝም ትላለህ፡፡
   - 4.3. የሠራኸው ሐጢአት ትንሽና ምንም እንዳይደለ ትቆጥራለህ፡፡ ከዚያም ከሠራኸው ሐጢአት ጋር ትኖራለህ፡፡
   - 4.4. ሰዎች ከሐጢአት ጋር ሲታገሉ አንተ ግን ወደ ቤተክርስቲያን ትገባለህ፡፡
   - 4.5. በእግዚአሔር ፊት መልካም በመሥራት እግዚአብሔር እንዲያድንህ ትፈልጋለህ፤ነገር ግን ሐጢአት በሠራህ ቁጥር ሁሌ ትጨነቃለህ፡፡
   - 4.6. በሐጢአት ምክንያት ሁል ጊዜ ማታለልና ውሸት አለ፡፡
5. ስለ ኢየሱስ ምን እንማራለን?

***ሀ.*** *የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት በቁ፡1 ላይ ‹ጠበቃ› ለሚለው ቃል ትርጉም ይሰጣል፡፡ ይህን ጠበቃ የሚለውን ቃል የግሪኩ ትርጉም ‹ፓራክሊቶስ› ይለዋል፡፡ የዚህ ቃል ትርጉም ለአንተ የሚሟገት ሰው (ጠበቃ) ማለት ነው፡፡ ይህ ቃል በፍርድ ቤት የሚጠቀም ቃል ሲሆን ለአንተ ጉዳይ ለሚሟገት ሰው የተሰጠ ስያሜ ነው፡፡ ኢየሱስ ጠበቃችን እንዲሆን ያስፈለገው ለምንድነው? ዕብ፡7፡25 አንብብ፡፡*

**ለ.** በቁ፡2 ላይ ‹‹ማስተሰሪያ›› የሚለውን ቃል እንማራለን፡፡ የዚህን ቃል ትርጉም የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት ሐጢአት የተሸፈነበት መንገድ እንደሆነና እግዚአብሔር ምህረቱን ለመግለጥ ለሐጢአት የተከፈለው ዋጋ እንደሆነ ይገልጻል፡፡ እግዚአብሔር ለሐጢአት በተከፈለው ዋጋ ደስ ተሰኝቷል፡፡ እኛም ሐጢአታችን ስለተሰረየልን ከእግዚአብሔር ጋር ግንኙነት ማድረግ እንችላለን፡፡ ለማን ሐጢአት ነው ዋጋ የተከፈለው? የሐጢአቱ መጠን ምን ያህል ነበር? ስለዚህ ኢየሱስ ራሱ ለሐጢአት መልስ እንደሆነ እንማራለን፡፡

6. ‹እናውቃለን› የሚለውን ቃል ፈልግ፡፡ እንዚህን ቃላቶች ከሥር አስምርባቸው፡፡ ‹እናውቃለን› ከሚለው ቃል ምን እንማራለን? እኛ ማወቅ የምንችለው ነገር ምንድነው? እንዴትስ እናውቀዋለን? ማርቲን ሉተር ክንግ የተባለው ሰው፡- ‹‹እኛ መሆን እንደምንመኘው መሆን አንችልም›› ብሏል፡፡ ወደፊትም ለመሆን የምንመኘውን መሆን አንችልም፡፡ ይሁን እንጂ እኛ ጌታን ከመቀበላችን በፊት የነበረን ማንነት አሁን ስለሌለን እግዚአብሔር ይመስገን፡፡

**ከሕይወት ጋር ማዛመድ**
በቁ፡6 ላይ እንደተቀሰው ሃሳብ መሠረት እንዴት መመላለስ እንችላለን? ኢየሱስ እንዴት ይመላለስ ነበር?
ከዚህ ታሪክ የተነሣ ሕይወትህ እንዴት መለወጥ አለበት?

# ትምህርት 4

## በብርሃን ትመላለሳለህ? (1ዮሐ፡2፡9-11)

**መሪው ድምጹን ከፍ አድርጎ መግቢያውን ያነባል፦**
ባለፈው ሳምንት ኢየሱስ ክርስቶስ የሐጢአታችን ማስተሰሪያ እንዳደረገ ተምረን ነበር፡፡ ይህም ማለት እኛ እርሱን እንደግል አዳኛችን አድርገን ስንቀበለው ሐጢአታችን በሙሉ በደሙ ይሸፈናል ማለት ነው፡፡ ደግሞም እርሱ የእኛ ጌታ ነው፡፡ ይህ በየዕለቱ የምንኖረውን ኑሮ ይቀይረዋል፡፡ ዛሬ በተጨማሪ በብርሃን ስለ መመላለስ እንማራለን፡፡

1ዮሐ፡2፡9-11 እንደገና ድምጽህን ከፍ አድርገህ አንብብ፡፡

ቁ፡9 በብርሃን አለሁ የሚል ወንድሙንም የሚጠላ እስከ አሁን በጨለማ አለ፡፡
ቁ፡10 ወንድሙንም የሚወድ በብርሃን ይኖራል፤ማሰናከያም የለበትም፤
ቁ፡11 ወንድሙን የሚጠላ ግን በጨለማ አለ፤በጨለማም ይመላለሳል፤የሚሄድበትንም አያውቅም፤ጨለማው አይኖቹን አሳውሮታልና፡፡

ክፍሉን እንደገና አንብበው፡፡ የተደጋገው ቃል የትኛው ነው? ይህንን ቃል የሚቃረነው ሀሳብ ምንድነው?

**የትርጉምና የውይይት ሀሳቦች**

1. በብርሃን የሚመላለሰውን ሰው ባህሪያትና በጨለማ የሚመላለሰውን ሰው ባህሪያት ከዚህ በታች ዘርዝር፡፡

| በብርሃን የሚመላለስ ሰው ባህሪያት | በጨለማ የሚመላለስ ሰው ባህሪያት |
| --- | --- |

2. ክርስቲያን ስለሆነውና ክርስቲያን ስላልሆነው ሰው አኗኗር ምን ትማራለህ? ማቴ፡7፡16-20 አንብብ፡፡

3. ግሦች አንድ ሰው የሚያደርገውን ድርጊትን ያሳያሉ፡፡ 1ዮሐ፡2፡9-11 እንደገና አንብብና ድርጊትን የሚያሳዩ ግሦችን ፈልግ፡-
‹‹የሚጠላ፣የሚወድ፣ይኖራል፣ይመላለሳል›› እነዚህን የመሳሰሉት ናቸው፡፡
እነዚህ ግሦች ሁል ጊዜ ወይም በየቀኑ ተደጋግሞ በሚደረግ (present Tense) አኳኋን ነው የተገለጹት፡፡ ይህም ማለት በየዕለቱ የምንኖረውን አኗኗር ማለት ነው፡፡ ይኼ አንድ ጊዜ ብቻ ተደርጎ የሚተው ሳይሆን በሕይወት ዘመን ሁሉ የሚደረግ ነው፡፡

4. ወንድሞቻችንን እንዴት ነው የምንወዳቸው? ስለዚህ ነገር ኢየሱስ ብዙ ነገሮችን ተናግሯል፡፡ በመጀመሪያ ስለ ደጉ ሳምራዊ ሰው ታሪክ ተናገረ፡፡ ደግሞም በሉቃ፡6፡31-35 ላይ ጠላቶቻችንን እንኳን እንድንወዳቸው ኢየሱስ አስተምሮናል፡፡ ጌታ ኢየሱስ በዮሐ፡15 ላይ ደቀመዛሙርቱ እርሱ እንደወደዳቸው እርስ በራሳቸው እንዲዋደዱ አዘዛቸው፡፡

**<u>ከሕይወት ጋር ማዛመድ</u>**
የሚከተሉትን ጥቅሶች አንብበህ ሌሎች ሰዎችን በተግባር መውደድ የምንችልባቸውን መንገዶችን **ተወያይ**፡፡

**ራስህን ጠይቅ፡-**
ሌሎችን ኢየሱስ እንደወደዳቸው እኔ እወዳቸዋለሁ ወይ? ፍቅሩ ገደብ የሌለው ስለሆነ ሁሉንም ይወዳል፡፡ ፍቅሩ ጥልቅ ስለሆነ ሐጢአተኞችን ያስጠጋል፡፡ ፍቅሩ ከፍተኛ ስለሆነ እኔን ከሐጢአት ጉድጓድ አውጥቶ አዲስ ሰው አደረገኝ፡፡ ፍቅሩ ሐጢአትን የሚደመስስና እንደገና የማይቆጥር ነው፡፡ በእግዚአብሔር ፊት የምመላለሰው ምልልስ የሚለካው እኔ ለሌሎች ክርስቲያኖች ባለኝ ፍቅር ነው፡፡ መበለቶችንና ወላጅ የሌላቸውን ልጆች ለመርዳት ፍቃደኛ ነኝ? ሐጢአተኞች ከሐጢአታቸው ንስሐ ገብተው ሲመለሱ በክርስቲያኖች ሕብረት ውስጥ ለመቀበል ዝግጁ ነኝ? ለሌሎች ክርስቲያኖች በታማኝነት እፀልያለሁ? በዚህ ሳምንት እግዚአብሔር በልብህ ላስቀመጣቸው ሰዎች እውነተኛ ፍቅርን እንድታሳይ መንፈስ ቅዱስ እንዲረዳህ ፀልይ፡፡

## <u>ትምህርት 5</u>

**<u>በብርሃን ትመላለሳለህ? 1ዮሐ፡2፡15-17</u>**

**<u>ለመሪው፡-</u> የሚከተሉትን ጥያቄዎች ቡድንህን ጠይቅ**፡፡ ባለፈው ሳምንት ምን ተምረሃል? የባለፈው ሳምንት ትምህርት በሕይወትህ ላይ ያመጣው ለውጥ ምንድነው?

1ዮሐ፡2፡15-17 አንብብ፡-

ቁ፡15 ዓለምን ወይም በዓለም ያሉትን አትውደዱ፤ማንም ዓለምን ቢወድ የአባት ፍቅር በእርሱ የለም።

ቁ፡16 በዓለም ያለው ሁሉ እርሱም የሥጋ ምኞትና የዓይን አምሮት ስለ ገንዘብም መመካት ከዓለም ነው እንጂ ከአባት አይደለም።

ቁ፡17 ዓለሙም ምኞቱም ያልፋል፤የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚያደርግ ለዘላለም ይኖራል።

<u>ምልከታ (የክፍሉን ሐሳብ ጠቅለል አድርጎ መመልከት)</u>

1. የተደጋገሙ ቃላቶች የትኞቹ ናቸው? የተደጋገሙ ቃላቶች የክፍሉን ትርጉም እንድናገኝ ይረዱናል። እነዚህን ቃላቶች ከዚህ በታች ዘርዝር። መልሱ፡- <u>አለም፣ምኞት</u>።
2. ዓለም ምንድነው? እኛ ከእግዚአብሔርን እንዳንወድ የሚያደርገን ነገር ሁሉ ዓለም ነው።
3. በቁ.17 ላይ ስለ ዓለም የተሰጠው እውነት ምንድነው?
4. ቁ፡16 ከአባት ያልሆኑ ነገር ግን ከዓለም የሆኑ ሦስት ነገሮችን ይዘረዝራል። እነዚህ ምንድናቸው?
5. በዘፍጥረት ላይ ያሉ ሁለት ታሪኮችን ብንመለከት እነዚህን ነገሮች የበለጠ መረዳት እንችላለን።

ሀ. ዘፍ፡3፡6 አንብብ። ሔዋን በአስደናቂው ገነት ውስጥ ሳለች ሰይጣን ፈተናት።

በ1ዮሐ፡2፡16 ላይ ያሉትን ሀሳቦች ከዘፍ፡3፡16 ላይ ካሉ ሀሳቦች ጋር አዛምድ።

ሴትዮዋ ዛፉ ለምግብነት ምቹ እንደሆነ አየች------------------------------------------

ለዓይን የሚያስጎመጅ መሆኑ---------------------------------------------------------

ደግሞም ያ ዛፍ ጥበብ እንደሚሰጥ---------------------------------------------------

4. በዘፍ፡11፡4 ሕዝቡ ምድርን እንዲሞሏት እግዚአብሔር አዘዘ። ይሁን እንጂ ሕዝቡ በአንድ ቦታ ብቻ ለመኖር ወሰነ።

ከዚያም፡- ‹‹ኑ፤ ለእኛ ከተማና ራሱ ወደ ሰማይ የሚደርስ ግንብ እንሥራ፤ በምድር ላይ ስማችንን እናስጠራው›› አሉ።

<u>የትርጉምና የውይይት ሀሳቦች</u>

1. ሕዝቡ በእግዚአብሔር ላይ ለማመጽ ፈለጉ። እነሱ ሊሠሩ ስለፈለጉት ግንብ ከፍተኛ ፍላጎት አደረባቸው። ለራሳቸው ስም ለማውጣት በከፍተኛ ሁኔታ ታበዩ። የአይን አምሮት፣የሥጋ ምኞትና ትዕቢታቸውን ታያለህ? ከትዕቢት በስተጀርባ ከሌሎች ከፍ ለማለት መፈለግና በውጪው ዓለም ለመደነቅ መፈለግ አለ። **ስለነዚህ ከላይ ስለተቀሱ ነገሮች ተወያይ።**
2. እግዚአብሔር ይህን የሚታየውን ዓለም ከፈጠረ በኋላ መልካም እንደሆነ አየ። ስለዚህ እግዚአብሔር ስለ ፈጠረው ፍጥረትና ስለ ድንቅ ስጦታው ደስተኞች ነን። ይሁን እንጂ ይህንን ዓለም እንዳንወድ እግዚአብሔር አስጠንቅቆናል። ዓለም በምን ዓይነት መንገድ ይፈታተነሃል?

3. ቁ፡17 እንደገና አንብብ፡፡ በዚህ ክፍል እርስ በርሳቸው የሚቃረኑ ሀሳቦች የትኞቹ ናቸው ‹ያልፋል› ሲል የሚያልፈው ምንድነው? ለዘላለም የሚኖረው ምንድነው? ለሚያልፍ ነገር መኖር ሞኝነት ነው ወይስ ጥበብ ነው?

<u>ከሕይወት ጋር ማዛመድ</u>

‹‹እነዚህ ነገሮች ከአባት አይደሉም፤ነገር ግን ከዓለም ናቸው፡፡›› ዓለም በአስተሳሰባችን ላይ ተጽዕኖ ያመጣና ሐጢአት ላይ እንድንወድቅ ሊያደርገን ይችላል፡፡ ስለዚህ ነገሮቻችን ከእግዚአብሔር ናቸው ወይስ ከዓለም የሚለውን ቆም ብለን ሊናጠነው ያስፈልጋል፡፡ አስተሳሰባችንን የምንገመግምባቸው ጥያቄዎች ከዚህ በታች ተቀምጠዋል፡-

1. ለስኬት ያለህ አስተሳሰብ ምንድነው? ሐዋሪያው ጳውሎስ እንደተራብ፣እንደተጠማ፣እንደሞተ እናውቃለን፡፡ ለእርሱ ተሳክቶለታል ትላለህ ወይስ አልተሳካለትም? ለምን?
2. ተቃራኒ ጾታ ሌላውን እንዲለምን የሚያደርገው ምንድነው? ይህ የእግዚአብሔር ሀሳብ ነው ወይስ የዓለም?
3. ገንዘብህን እንዴት ትጠቀማለህ? በእግዚአብሔር ምሪት ነው ወይስ በዓለም ተጽዕኖ ሥር ነህ?
4. የልብስ መደብሮችን ተመልከት፡፡ የሴቶች ልብስ አሠራር እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ነው ወይስ የዓለምን ፋሽን ይከተላል? በልብሶቻቸው ወንዶች ይፈተናሉ?

## <u>ትምህርት 6</u>

### <u>በብርሃን ትመላለሳለህ? 1ዮሐ፡2፡18-29</u>

***መሪው ድምጹን ከፍ አድርጎ መግቢያውን ያነባል፡-*** ዛሬ የምናነበው ክፍል ለመረዳት የሚያስቸግር ነው፡፡ ይህንን ክፍል ደጋግመን ማንብብና እግዚአብሔር እንዲያስተምረን መፀለይ አለብን፡፡ ስለዚህ እነዚህን አቅጣጫዎች በትዕግስት መከታተል አለባችሁ፡፡ እግዚአብሔር የሚያስተምርህን ለማዳመጥ ጥረት አድርግ፡፡

**<u>ምልከታ</u>**

ክፍሉን ስታነብ <u>‹‹**ጸንተው በኖሩ---**››፣‹‹**ጸንቶ ይኑር---**››</u> የሚሉ ቃላቶችን ልብ በል፡፡ እነዚያን ቃላቶች ከሥር ልታሰምርባቸው ትችላለህ፡፡ **ጸንተው ይኑር** ማለት ምን ማለት ነው ይህም በቤት ውስጥ መኖር ለሚለው የተጠቀመ ቃል ነው፡፡

ቁ፡18 ልጆች ሆይ መጨረሻው ሰዓት ነው የክርስቶስም ተቃዋሚ ይመጣ ዘንድ እንደ ሰማችሁ አሁን እንኳ ብዙዎች የክርስቶስ ተቃዋሚዎች ተነሥተዋል፤ስለዚህም መጨረሻው ሰዓት እንደሆነ እናውቃለን።
ቁ፡19 ከእኛ ዘንድ ወጡ ዳሩ ግን ከእኛ ወገን አልነበሩም፤ ከእኛ ወገንስ ቢሆኑ ከእኛ ጋር **ጸንተው በኖሩ** ነበር፤ ነገር ግን ሁሉ ከእኛ ወገን እንዳልሆኑ ይገለጡ ዘንድ ወጡ።
ቁ፡20 እናንተም ከቅዱሱ ቅባት ተቀብላችኋል ሁሉንም ታውቃላችሁ።
ቁ፡21 እውነትን የምታውቁ ስለ ሆናችሁ ውሸትም ሁሉ ከእውነት እንዳልሆነ ስለምታውቁ እንጂ እውነትን ስለማታውቁ አልጽፍላችሁም።
ቁ፡22 ክርስቶስ አይደለም ብሎ ኢየሱስን ከሚክድ በቀር ውሸተኛው ማን ነው? አብንና ወልድን የሚክድ ይህ የክርስቶስ ተቃዋሚ ነው።
ቁ፡23 ወልድን የሚክድ ሁሉ አብ እንኳ የለውም፤ በወልድ የሚታመን አብ ደግሞ አለው።
ቁ፡24 እናንተስ ከመጀመሪያ የሰማችሁት በእናንተ ጸንቶ ይኑር። ከመጀመሪያ የሰማችሁት በእናንተ ቢኖር እናንተ ደግሞ በወልድና በአብ ትኖራላችሁ።
ቁ፡25 እርሱም የሰጠን ተስፋ ይህ የዘላለም ሕይወት ነው።
ቁ፡26 ስለሚያስቱአችሁ ሰዎች ይህን ጽፌላችኋለሁ።
ቁ፡27 እናንተስ ከእርሱ የተቀበላችሁት ቅባት በእናንተ ይኖራል፤ማንም ሊያስተምራችሁ አያስፈልጋችሁም፤ ነገር ግን የእርሱ ቅባት ስለ ሁሉ እንደሚያስተምራችሁ፣ እውነተኛም እንደ ሆነ ውሸትም እንዳልሆነ ፣ እናንተንም እንዳስተማራችሁ፣ በእርሱ ኑሩ።
ቁ፡28 አሁንም፣ ልጆች ሆይ፣ በሚገለጥበት ጊዜ እምነት እንዲሆንልን በመምጣቱም በእርሱ ፊት እንዳናፍር በእርሱ ኑሩ።
ቁ፡29 ጻድቅ እንደ ሆነ ካወቃችሁ ጽድቅን የሚያደርግ ሁሉ ከእርሱ እንደተወለደ እወቁ።

**ምልከታ**

እንዲገባችሁና ክፍሉን መተርጎም እንድትችል በጥንቃቄ አንብብ።

1. በእነዚህ ከላይ በተጠቀሱ ጥቅሶች ውስጥ ‹ጸንቶ መኖር› ማለት ምን ማለት ነው?
2. ቁ፡23 እንደገና አንብብ። ኢየሱስ ልጅ እንደሆነ ካወቅህ ለአንተ ማን አለህ?
3. ቁ፡22 እንደገና አንብብ። እውነተኛ ክርስቲያን ለመሆን ከፈለክ ስለ ኢየሱስ ማወቅ ያለብህ እውነት ምንድነው? ስለዚህ ስለ ኢየሱስ በቀጣይነት ማመን ያለብህ ምንድነው?
4. በቁ፡24 መሠረት ስለ ኢየሱስ እውነትን የምታውቅ ከሆንክ ለዚህ ውጤቱ ምን ይሆናል?
5. በእግዚአብሔር ላይ እምነትህን ስለጣልክ እግዚአብሔር ለአንተ የሚሰጠው ተስፋ ምንድነው? ቁ፡25
6. በቁ፡28 ላይ የተሰጠው ትዕዛዝ ምንድነው? ለዚህ ትዕዛዝ ሐዋሪያው ዮሐንስ የሚሰጠው ምክንያት ምንድነው?
7. ከቁ፡18-23 ያለውን ክፍል እንደገና አንብብና ‹የክርስቶስ ተቃዋሚ› የሚሉትን ቃላቶች ፈልግ። ከዚህ ምን ትማራለህ? የክርስቶስ ተቃዋሚዎች የትኞቹ ናቸው? እነርሱ የሚክዱት እውነት ምንድነው?

8. በሚከተሉት ጥቅሶች ውስጥ የእውነተኛ ክርስቲያን ባህሪያትን ዘርዝር፡፡
   ሀ. ቁ፡19
   ለ. ቁ፡20
   ሐ. ቁ፡21
   መ. ቁ፡23
   ሠ. ቁ፡24
   ረ. ቁ፡25
   ሰ. ቁ፡27 (ሁለት ነገሮች)
   ሸ. ቁ፡28
   ቀ. ቁ፡29 (ሁለት ነገሮች)
9. ጽድቅ ማለት ትክክል የሆነውን ማድረግ ማለት ነው፡፡ ይህም ማለት ሕይወትህ ተለውጦ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ መኖር ማለት ነው፡፡ ቁ፡29 እንደገና አንብብ፡፡ በጽድቅ መኖር የሚችል ማነው?

**<u>ትርጉም፡</u>**

1. የክርስቶስ ተቃዋሚዎች እንዴት ቤተክርስቲያንን ያታልሏታል? ሐዋ፡20፡29-30 አንብብ፡፡
2. ከቁ.21-23 እንደገና አንብብ፡፡ እነሱ የሚያውቁት እውነት ምን ነበር? የኢየሱስ ክርስቶስን ጌትነት መመስከር ማለት ምን ማለት ነው?

**<u>ከሕይወት ጋር ማዛመድ</u>**

ዛሬ የተማርካቸው አዲስ ነገሮች ምንድናቸው? መጠየቅ የምትፈልገው ጥያቄ አለ? ካለህ ከዚህ በታች ጻፍ፡-

በሚቀጥለው ሳምንት ክፍሉን ሳትተው አንብብ፡፡ ከዚያም እግዚአብሔር ለጥያቄዎችህ ምላሽ እንዲሰጥ ለምነው፡፡

## <u>ትምህርት 7</u>

### <u>በብርሃን ትመላለሳለህ? (1ዮሐ፡3፡1-12)</u>

**<u>ድምጽህን ከፍ አድርገህ መግቢያውን አንብብ፡-</u>** ባለፈው ሳምንት ክርስቲያኖች በጌታ ጸንተው መኖራቸውን ተምረን ነበር፡፡ መንፈስ ቅዱስ በአንተ ውስጥ ጸንቶ ስለሚኖር እውነትን ያስተምርሃል፡፡ ምናልባት ከእግዚአብሔር ከአባትህ ወደ ኋላ አፈግፍገህ ሊሆን ይችላል፤ነገር ግን እንደገና ይመልስሃል፤ምክንያቱም አንተ ዳግመኛ የተወለድክ ልጁ ነህ፡፡ በዚህ ሳምንት በተጨማሪ የእግዚአብሔር ልጅ ባህሪያት የትኞቹ እንደሆኑ እንማራለን፡፡

1ዮሐ፡3፡1-12 አንብብ፡-

ቁ1፡ የእግዚአብሔር ልጆች ተብለን ልንጠራ አብ እንዴት ያለውን ፍቅር እንደ ሰጠን እዩ፣ እንዲሁም ነን፡፡ ስለዚህ ምክንያት ዓለም እርሱን ስላላወቀው እኛን አያውቀንም፡፡
ቁ2፡ ወዳጆች ሆይ ፣ አሁን የእግዚአብሔር ልጆች ነን፣ ምንም እንደምንሆን ገና አልተገለጠም፡፡ ዳሩ ግን ቢገለጥ እርሱ እንዳለ እናየዋለንና እርሱን እንድንመስል እናውቃለን፡፡
ቁ3፡ በእርሱም ይህ ተስፋ የሚያደርግ ሁሉ እርሱ ንጹሕ እንደ ሆነ ራሱን ያነጻል፡፡
ቁ4፡ ሐጢአትን የሚያደርግ ሁሉ ዓመፅን ደግሞ ያደርጋል፣ ሐጢአትም ዓመፅ ነው፡፡
ቁ5፡ እርሱም ሐጢአትን ሊያስወግድ እንደ ተገለጠ ታውቃላችሁ፣ በእርሱም ሐጢአት የለም፡፡
ቁ6፡ በእርሱ የሚኖር ሁሉ ሐጢአትን አያደርግም፤ ሐጠአትን የሚያደርግ ሁሉ አላየውም አላወቀውምም፡፡
ቁ7፡ ልጆች ሆይ፣ማንም አያስታችሁ፣ እርሱ ጻድቅ እንደሆነ ጽድቅን የሚያደርግ ጻድቅ ነው፡፡
ቁ8፡ ሐጠአትን የሚያደርግ ከዲያብሎስ ነው፣ ዲያብሎስ ከመጀመሪያ ሐጥአትን ያደርጋልና፡፡
ቁ9፡ ስለዚህ የዲያብሎስን ሥራ እንዲያፈርስ የእግዚአብሔር ልጅ ተገለጠ፡፡ ከእግዘአብሔር የተወለደ ሁሉ ሐጢአትን አያደርግም፣ ዘሩ በእርሱ ይኖራልና፤ ከእግዚአብሔርም ተወልዷልና ሐጢአትን ሊያደርግ አይችልም፡፡
ቁ10፡ የእግዚአብሔር ልጆችና የዲያብሎስ ልጆች በዚህ የተገለጡ ናቸው፤ጽድቅን የማያደርግና ወንድሙን የማይወድ ሁሉ ከእግዚአብሔር አይደለም፡፡
ቁ11፡ ከመጀመሪያ የሰማችኋት መልእክት፡- እርስ በርሳችን እንዋደድ የምትል ይህች ናትና፤
ቁ12፡ ከክፉው እንደ ነበረ ወንድሙንም እንደ ገደለ እንደ ቃየል አይደለም፤ ስለ ምንስ ገደለው? የገዛ ሥራው ክፉ የወንድሙም ሥራ ጽድቅ ስለ ነበረ ነው፡፡

<u>**ምልከታ**</u>

1. 1ዮሐ፡3፡1-12 እንደገና አንብብ፡፡ ስታነብ <u>‹የእግዚአብሔር ልጆች›</u> የሚለውንና <u>‹የዲያብሎስ ልጆች›</u> የሚለውን ሀረግ ፈልገህ አግኝ፡፡
2. ከዚህ በታች ዘርዝር፡፡

| <u>የእግዚአብሔር ልጆች</u> | <u>የዲያብሎስ ልጆች</u> |
|---|---|

3. ቁ፡ 3 እንደሚለው የእግዚአብሔር ልጆች የሆኑት ምን ያደርጋሉ?
4. በዚህ ምዕራፍ ላይ ያሉ የድርጊት አመልካቾች (ግሦች) የተገለጹበት ጊዜ እግዚአብሔር ሊያስተምረን የፈለገውን ነገር እንድንረዳ ስለሚያደርጉ በጣም

አስፈላጊ ናቸው፡፡ ለምሳሌ፡- ‹ያደርጋል› የሚለው ቃል አንድ ጊዜ ብቻ የሚደረግ ሳይሆን ቀጣይነት ያለው ልማድ ነው፡፡ ይህም ማለት በባሕሪይ ወይም በአኗኗር ለውጥ አያመጣም ማለት ነው፡፡ በቁ. 6 ላይ ‹ሐጢአት ያደርጋል› የሚለው ሀረግም አንድ ጊዜ ብቻ ተደርጎ የሚተው ሳይሆን ሁል ጊዜ በሚደረግ አገላለጽ ነው የተገለጸው፡፡ ይህ ምን ይነግርሃል?

5. የእግዚአብሔር ልጅ ሐጢአት ያደርጋልን? 1ዮሐ፡2፡1 እንደገና አንብብ፡፡ ይህ ‹ሐጢአት ያደርጋል› የሚለው ሀረግ የድርጊት አመልካች (ግሥ) በተለያዩ ጊዜአቶች የሚገለጽ ነው፡፡ የእግዚአብሔር ልጅ የሚያደርገው ሐጢአትና የዲያብሎስ ልጅ የሚያደርገው ሐጢአት ልዩነቱ ምንድነው?
6. ስለ እግዚአብሔር ልጅ በቁ፡9 ምን ትማራለህ?
7. ስለታወቁ የዲያብሎስ ልጆች ባሕሪያት ቁ፡10 ምን ያስተምረናል?

**ትርጉምና የውይይት ሀሳብ**

ከእነዚህ ጥቅሶች በመነሳት አንድ ሰው አባቱ ማን እንደሆነ እንዴት ሊያውቅ ይችላል?

**ከሕይወት ጋር ማዛመድ**

በዚህ ዓለም ስንኖር ክርስቲያን ማነው? የሚለው ሀሳብ ሲነሳ ግራ ያጋባል፡፡ ነገር ግን እግዚአብሔር ግራ አይገባውም፡፡ በዚህ መጽሐፍ ላይ ክርስቲያንና ክርስቲያን ያልሆነው ማን እንደሆነ በግልጽ ይነግረናል፡፡ የእግዚአብሔር ልጅ የሆነ በሕይወቱ የመታዘዝ፣ሌሎችን የመውደድና እግዚአብሔርን የማወቅ ጥበብ አለው፡፡ አዲስ ክርስቲያን እስኪለወጥ ጥቂት ጊዜ ሊወስድበት ይችል ይሆናል፡፡ ነገር ግን ዳግመኛ የተወለደ ከሆነ አዲስ ልብ ስላለው ሕይወቱ ይለወጣል፡፡ አማኝ የሆነ ሰው ከሚሠራው ሐጢአት ተጸጽቶ ወደ እግዚአብሔር ይመለሳል፡፡ ጠላታችን ሰይጣን በውሸት እንደሚያታልልህ አትዘንጋ፡፡

1. ሐጢአትን ለሚለማመድ ክርስቲያን ሰይጣን ምን ዓይነት ማታለያዎችን ሊያቀርብ ይችላል?
2. ክርስቲያን ሳይሆን ክርስቲያን ነኝ ለሚል ሰው ደግሞ ሰይጣን ምን ዓይነት ማታለያዎችን ሊያቀርብ ይችላል?
3. በእነዚህ ጥቅሶች መሠረት እግዚአብሔር ከራሱ ጋር ግንኙነት እንዳለህ እንድታውቅ እንደሚፈልግ ይገባሃል? አንተ እውነተኛ ክርስቲያን ነህ? ወደ ቤተክርስቲያን መሄድ ብቻውን ክርስቲያን ሊያደርግህ አይችልም፡፡ ታምር ብትሠራ እንኳን ክርስቲያን ላትሆን ትችላለህ፡፡ ጌታ ኢየሱስ በማቴ፡ 7 ላይ ‹‹በፍሬያቸው ታውቋቸዋላችሁ›› ብሏል፡፡ በየዕለቱ በምትኖረው አኗኗር፣በአስተሳሰብህና በአነጋገርህ ኢየሱስን ለመምሰል ጥረት እያደረግክ ነህ? ሰይጣን እንዲያታልልህ እድል ፋንታ አትስጠው፡፡

## ትምህርት 8

**በብርሃን ትመላለሳለህ? (1ዮሐ፡3፡13-14)**

**መግቢያውን አንብብ፡-** ባለፈው ሳምንት እግዚአብሔር አባታችን እንደሆነ የምናውቅበትን ክፍል ተምረን ነበር፡፡ ዳግም መወለዳችንን ሕይወታችን ይመሰክራል፡፡ በዚህ ሳምንት

ምዕራፍ ሦስትን እንጨርሳለን፡፡ ፍቅር የሚለው ቃል ተደጋግሟል፡፡ የግሪኩ ትርጉም ፍቅርን ‹አጋፔ› ይለዋል፡፡ ይህም ማለት በሁኔታዎች የማይለዋወጥ ፍቅር ማለት ነው፡፡ ይህም ማለት ለሌሎች ከሁሉም የተሻለውን ነገር የሚያስብ ማለት ነው፡፡ ይህም አንድ ሰው ሠርቶ ለሥራው የሚያገኘው ክፍያ ሳይሆን እንድሁ በነፃ የሚሰጥ ነው፡፡ ዘላቂና ቋሚ ነው፡፡
ከዚህ በታች ያሉትን ጥቅሶች አንብብና ‹‹ፍቅር›› የሚለውን ቃል ፈልግ፡፡

ቁ13 ወንድሞች ሆይ ፣ ዓለም ቢጠላችሁ አትደነቁ፡፡
ቁ14 እኛ ወንድሞችን የምንወድ ስለ ሆነነ ከሞት ወደ ሕይወት እንደ ተሻገርን እናውቃለን፡፡ ወንድሙን የማይወድ በሞት ይኖራል፡፡
ቁ15 ወንድሙን የሚጠላ ሁሉ ነፍሰ ገዳይ ነው፣ ነፍሰ ገዳይም የሆነ ሁሉ የዘላለም ሕይወት በእርሱ እንዳይኖር ታውቃላችሁ፡፡
ቁ16 እርሱ ስለ እኛ ነፍሱን አሳልፎ ሰጥቷልና በዚህ ፍቅርን አውቀናል፤ እኛም ስለ ወንድሞቻችን ነፍሳችንን አሳልፈን እንድንሰጥ ይገባናል፡፡
ቁ17 ነገር ግን የዚህ ዓለም ገንዘብ ያለው፣ወንድሙም የሚያስፈልገው ሲያጣ አይቶ ያልራራለት ማንም ቢኖር የእግዚአብሔር ፍቅር በእርሱ እንዴት ይኖራል?
ቁ18 ልጆቼ ሆይ ፣ በሥራና በእውነት እንጂ በቃልና በአንደበት አንዋደድ፡፡
ቁ19 እና 20 ልባችንም በእኛ ላይ በሚፈርድበት ሁሉ፣ ከእውነት እንደሆንን በዚህ እናውቃለን በፊቱም ልባችንን እናሳርፋለን፣ እግዚአብሔር ከልባችን ይለውቀ ታላቅ ነውና ሁሉንም ያውቃል፡፡
ቁ21 ወዳቾች ሆይ፣ ልባችንስ ባይፈርድብን በእግዚአብሔር ዘንድ ድፍረት አለን፣
ቁ22 ትእዛዙንም የምንጠብቅና በፊቱ ደስ የሚያሰኘውን የምናደርግ ስለ ሆንን የምንለምነውን ሁሉ ከእርሱ እናገኛለን፡፡
ቁ23 ትዕዛዚቱም ይህች ናት፣ በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እናምን ዘንድ ፣ ትዕዛዝንመ እንደ ሰጠን እርስ በርሳችን እንዋደድ ዘንድ፡፡
ቁ24 ትዕዛዙንም የሚጠብቅ በእርሱ ይኖራል እርሱም ይኖርበታል፤ በዚህ በእኛ እንዲኖር ከሰጠን ከመንፈሱ እናውቃለን፡፡

<u>ምልከታ</u>

1. ፍቅር የሚለውን ቃል በዚህ ክፍል ተመልከት፡፡ ስንት ጊዜ ነው የተደጋገመው? ስለ ፍቅር ጥቅም ከዚህ ክፍል ምን ትማራለህ?
2. የሚከተለውን ባዶ ቦታ ሙላ፡፡
   ሀ. ወንድሞችን የምንወድ ከሆነ ከሞት ወደ--------------------- ተሻግረናል፡፡ (ቁ.14)
   ለ. ሌሎችን የምትጠላ ከሆነ በ----------------------------እንኖራለን፡፡ (ቁ.14)
   ሐ. ወንድሞቻችንን የምንወድ ከሆንን ለወንድሞቻችን -------------------------- እንሰጣለን፡፡(ቁ.16)
   መ. ወንድሞቻችንን ስንወድ በእውነትና በ--------------------------------- መሆን አለበት፡፡ (ቁ.18)
   ሠ. እግዚአብሔር -----------------------------------እንድናደርግ አዝዞናል፡፡ (ቁ.23)
3. በእነዚህ ክፍሎች መሠረት ፍቅርን እንዴት ማሳየት እንችላለን?
4. ቁ15 ምን ያስተምረናል?
5. ለአጋፔ (የማይለወጠው ፍቅር) ታላቁ ምሳሌያችን ማነው?

6. ቁ19 እንደገና አንብብ። ከዚህ ምን እናውቃለን? ይህ ሥፍራ ከቁ17 እና 18 ጋር እንዴት ይገናኛል?
7. በቁ23 የተገለጹ ሁለት ትዕዛዛት ምንድናቸው?

## የትርጉምና የውይይት ጥያቄዎች

1. ቁ19-24 እንደገና አንብብ። እግዚአብሔር በፊቱ ድፍረት እንዲኖረን ይፈልጋል። ይህ ምን ማለት ነው? ድፍረት እንዴት በልባችን ሊኖረን ይችላል?
2. ቁ22 ተነጥሎ ሊታይ አይችልም። ‹‹…የምንለምነውን ሁሉ ከእርሱ እናገኛለን›› የሚለውን የልመና ርዕስ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለ ልመና የሚናገሩ ሌሎች ክፍሎች ጋር አስተያይና የትርጉም እርማት አድርግ። ቁ22ን ከሌሎች ክፍሎች ጋር ሚዛናዊ ማድረግ አለብን። 1ዮሐ፡5፡14ን አንብብ። ይህ ቦታ መልስን ስላስገኘ ፀሎት ይናገራል።

## ከሕይወት ጋር ማዛመድ

1. ዛሬ አዲስ የተማርከው ነገር ምንድነው?
2. ከዚህ ጥናት የተነሣ ሕይወትህ በዚህ ሳምንት እንዴት መለወጥ አለበት?

# ትምህርት 9

## በብርሃን ትመላለሳለህ? (1ዮሐ፡4፡1-6)

**ድምጽህን ከፍ አድርገህ መግቢያውን አንብብ፦** ባለፈው ሳምንት እውነተኛ ክርስቲያን ሌሎችን እንደሚወድ ተምረን ነበር። ፍቅር ለእግዚአብሔር በጣም ወሳኝ ነገር ነው። ስለፍቅር ብዙ ከመማራችን በፊት ሐዋሪያው ዮሐንስ እኛን ስለ ሚያታልሉን ሰዎች ይጽፍልናል።

**1ዮሐ፡4፡1-6 አንብብ**ና ‹መንፈስ› የሚለውን ስታገኝ የክብ ምልክት አድርግበት።

ቁ.1 ወዳጆች ሆይ፣ መንፈስን ሁሉ አትመኑ፣ ነገር ግን መናፍስት ከእግዚአብሔር ሆነው እንደ ሆነ መርምሩ፤ ብዙዎች ሐሰተኞች ነቢያት ወደ ዓለም ወጥተዋልና።
ቁ.2 የእግዚአብሔርን መንፈስ በዚህ ታውቃላችሁ፤ ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ እንደ መጣ የሚታመን መንፈስ ሁሉ ከእግዚአብሔር ነው።
ቁ.3 ኢየሱስ ክርስቶስም በሥጋ እንደ መጣ የማይታመን መንፈስ ሁሉ ከእግዚአብሔር አይደለም፤ ይምም የክርስቶስ ተቃዋሚው መንፈስ ነው፤ ይህም እንዲመጣ ሰምታችኋል፣ አሁንም እንኳ በዓለም አለ።
ቁ.4 ልጆች ሆይ፣ እናንተ ከእግዚአብሔር ናችሁ አሸንፋችኋውማል፣ በዓለም ካለው ይልቅ በእናንተ ያለው ታላቅ ነውና።
ቁ.5 እነርሱ ከዓለም ናቸው፤ስለዚህ ከዓለም የሆነውን ይናገራሉ ዓለሙም ይሰማቸዋል።
ቁ.6 እኛ ከእግዘአብሔር ነን፤ እግዚአብሔርን የሚያውቅ ይሰማልና፤ ከእግዚአብሔር ያልሆነ አይሰማንም። የእውነትን መንፈስና የስሕተትን መንፈስ በዚህ እናውቃለን።

ቁ.1-6 ድረስ ያለውን እንደገና አንብብና <u>‹ዓለም›</u> በሚለው ቃል ሥር አስምርበት፡፡

**<u>ምልከታ</u>**

1. መንፈስ ስለ ሚለው ቃል ምን ትማራለህ? ከዚህ ሀሳብ ጋር የሚቃረን ሀሳብ ምንድነው?

| <u>ከእግዚአብሔር የሆነ መንፈስ</u> | <u>ከእግዚአብሔር ያልሆነ መንፈስ</u> |
|---|---|
| ቁ.2 | ቁ.1 |
| ቁ.6 | ቁ.3 |
| ቁ.4 | ቁ.3 |
| | ቁ.5 |

2. የሚበልጠው የትኛው ነው? ቁ.4ን እንደገና ተመልከት፡፡
3. አንተ እንድታውቅ እግዚአብሔር የሚፈልገው ምንድነው?

   ሀ. ቁ.2 በዚህ ------------------------------------አውቃለሁ፡፡
   ለ. ቁ.6 ----------------- እና -------------------------መንፈስ በዚህ አውቃለሁ፡፡

**<u>የትርጉምና የውይይት ጥያቄዎች</u>**

4. አንድ ሰው ይህ መልዕክት ከእግዚአብሔር ነው ስላለ ብቻ አንድን ነገር ማመን የለብንም፡፡ በቤተክርስቲያን ዛሬ ሐሰተኛ ነቢያቶች አሉ፡፡ ስለዚህ የሚመጣውን መልዕክት በሙሉ የምንመረምርበት መንገድ አለ፡፡
   ሀ. መልዕክታቸው ከመጽሐፍ ቅዱስ ሀሳብ ጋር ይስማማል ወይ? የእግዚአብሔር ሀሳብ እርስ በርስ አይጋጭም፡፡
   ለ. አስተማሪው ምን ያህል ነው ራሱን የሰጠው? አኗኗሩንና ሕይወቱን ተመልከት፡፡
   ሐ. ስለ ክርስቶስ የሚያምኑት ምንድነው? ኢየሱስ አምላክም ሰውም እንደሆነ ያስተምራሉ?
   መ. ይህ መመርመር የሚለው በ1ዮሐ፡ ላይ መንፈስን እንጂ ሰውን አያሳይም፡፡
   ሠ. ተናጋሪው ሰዎች ከእሱ ይልቅ ኢየሱስን እንዲያዩ ያደርጋል? ክብሩን የሚወስደው ማንነው? እግዚአብሔር ክብሩን ለሰዎች አያጋራም (ት/ኢሳ፡42፡8)፡፡
5. ሐሰተኛ አስተማሪዎች ለሰዎች ጆሮ የሚመቸውን ብቻ ስለሚናገሩ የታወቁ ይሆናሉ፡፡ 2ጢሞ፡3፡1-5 ያለውን አንብብና ሰዎች ለምን እውነትን መስማት እንደማይፈልጉ ተወያይ፡፡

**<u>ከሕይወት ጋር ማዛመድ</u>**

6. የሐሰት አስተማሪዎች ዛሬ ለቤተክርስቲያን የሚናገሩቸው ሁለት ማታለያዎች ከዚህ በታች ተጠቅሰዋል፡-
   ሀ. እግዚአብሔር የይቅርታ አምላክ ስለሆነ የምትፈልጉትን ሐጢአት ሁሉ ማድረግ ትችላላችሁ፡፡
   ለ. ሐጢአት ብትሠሩ ደህንነታችሁን ታጣላችሁ፡፡
   ሐ. ሌሎች ማታለያዎች ምንድናቸው?

7. በእነሱ እንዳንታለል ሊረዳን የሚችለው ምንድነው?

እግዚአብሔር ጥበብና እውነትን እንድታውቁ እንዲረዳችሁ በመፀለይ የዛሬውን ክፍለ ጊዜ አጠናቅቁ፡፡

## <u>ትምህርት 10</u>

**<u>በብርሃን ትመላለሳለህ? (1ዮሐ፡4፡7-21)</u>**

***ድምጽህን ከፍ አድርገህ መግቢያውን አንብብ፡-*** *ሁሉም ሰው ፍቅር አስፈላጊ እንደሆነ ያስባል፡፡ ሰዎች ፍቅርን ሲያገኙ ደስ ይላቸዋል፤ይበረታታሉ፤ደግሞም ሌሎችን ለመውደድ ይነሳሳሉ፡፡ አንዳንድ ሰዎች ፍቅር ስሜታዊ ስለ ሆነ ይመጣል፤ይሄዳሉ ይላሉ፡፡ ግን ራስ ወዳድ ያልሆነ ፍቅር ቋሚ ነው፡፡ ዛሬ የመጽሐፉን ክፍል አንብብና ፍቅር የሚለው ቃል ስንት ጊዜ እንደተገለጸ ቁጠር፡፡*

ከቁ.7-21 *ያለውን ክፍል አንብብና ፍቅር በሚለው ቃል ሥር አስምርበት፡፡*
ቁ.7 ወዳጆች ሆይ ፣ ፍቅር ከእግዚአብሔር ስለ ሆነ፣ የሚወደውም ሁሉ ከእግዚአብሔር ስለ ተወለደ እግዚአብሔርንም ስለሚያውቅ፣ እርስ በርሳችን እንዋደድ፡፡
ቁ.8 ፍቅር የሌለው እግዚአብሔርን አያውቅም፣ እግዚአብሔር ፍቅር ነውና፡፡
ቁ.9 በዚህ የእግዚአብሔር ፍቅር በእኛ ዘንድ ተገለጠ፣በእርሱ በኩል በሕይወት እንኖር ዘንድ እግዚአብሔር አንድ ልጁን ወደ ዓለም ልኮታልና፡፡
ቁ.10 ፍቅረም እንደዚህ ነው፡፡ እግዚአብሔር እርሱ ራሱ እንደ ወደደን ስለ ሐጢአታችንም ማስተስሪያ ይሆን ዘንድ ልጁን እንደ ላከ እንጂ እኛ እግዚአብሔርን እንደ ወደድነው አይደለም፡፡
ቁ.11 ወዳጆች ሆይ እግዚአብሔር እንዲህ አድርጎ ከወደደን እኛ ደግሞ እርስ በርሳችን ልንዋደድ ይገባናል፡፡
ቁ.12 እግዚአብሔርንም ማንም ከቶ አላየውም፤ እርስ በርሳችን ብንዋደድ እግዚአብሔር በእኛ ይኖራል ፍቅሩም በእኛ ፍጹም ሆኖአል፡፡
ቁ.13 ከመንፈሱ ስለ ሰጠን፣ በእርሱ እንድንኖር እሱም በእኛ እንዲኖር በዚህ እናውቃለን፡፡
ቁ.14 እኛም አይተናል አባትም ልጁን የዓለም መድሃኒት ሊሆን እንደላከው እንመሰክራለን፡፡
ቁ.15 ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆነ በሚታመን ሁሉ እግዚአብሔር በእርሱ ይኖራል እርሱም በእግዚአብሔር ይኖራል፡፡
ቁ.16 እኛም እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን ፍቅር አውቀናል አምነንማል፡፡ እግዚአብሔር ፍቅር ነው ፣ በፍቅርም የሚኖር በእግዚአብሔር ይኖራል እግዚአብሔርም በእርሱ ይኖራል፡፡
ቁ.17 በፍርድ ቀን ድፍረት ይሆንልን ዘንድ ፍቅር በዚህ ከእኛ ጋር ተፈጽሞአል፤እርሱ እንዳለ እኛ ደግሞ እንዲሁ በዚህ ዓለም ነንና፡፡

ቁ.18 ፍጹም ፍቅር ፍርሃትን አውጥቶ ይጥላል እንጂ በፍቅር ፍርሃት የለም፣ ፍርሃት ቅጣት አለውና የሚፈራም ሰው ፍቅሩ ፍጹም አይደለም።
ቁ.19 እርሱ አስቀድሞ ወዶናልና እኛ እንወደዋለን።
ቁ.20 ማንም፦ እግዚአብሔርን እወዳለሁ እያለ ወንድሙን ቢጠላ ሐሰተኛ ነው፤ያየውን ወንድሙን የማይወድ ያላየውን እግዚአብሔርን ሊወደው እንዴት ይችላል?

__ምልከታ (የክፍሉን ሀሳብ ጠቅለል አድርጎ መመልከት)__

1. በቁ.7 ላይ ስለ ፍቅር ምን እንማራለን? ማንን መውደድ አለብን?
2. ሀተ
3. እግዚአብሔር------------- ነው። ቁ.8
4. እርስ በርሳችን መዋደድ ለምን አስፈለገ? ቁ.11
5. እግዚአብሔር እንደወደደን ሌሎችን እንድንወድ የሚረዳን ማነው? ቁ.13 እና 14 በተጨማሪም ሮሜ፡5፡5ን አንብብ።
6. በፍርድ ቀን ድፍረት እንዲኖረን እንዴት ማድረግ እንችላለን? ቁ.17
7. እኛ ከእግዚአብሔር ለመሆናችን ማረጋገጫው ምንድነው?
8. ደህንነታችሁን አጥታችሁ በፍርሃት እንድትኖሩ እግዚአብሔር ይፈልጋልን? ቁ.8

__የትርጉምና የውይይት ጥያቄዎች__

1. እግዚአብሔር ፍቅር ነው ሲባል ሐጢአትን ይረሳል ወይም ሸፍኖ ያልፋል ማለት ነው? ቁ.10 እና 14
2. ቁ.21ን አንብብ። እግዚአብሔር በአማኞች ፍቅር ላይ ትኩረት ያደርጋል:: የእግዚአብሔር ሕዝብ በዓለም ላይ ለውጥ ለማምጣት ቁልፍ ሚና ይጫወታል። ለምን አማኞች ብቻ የእግዚአብሔርን ፍቅር ለሌሎች ያካፍላሉ? የእግዚአብሔር ሕዝብ በቤተክርስቲያን ውስጥ እርስ በርስ ቢዋደድ ምን ይሆናል?

__ከሕይወት ጋር ማዛመድ__

1. ሌሎችን እንወዳለን ማለት ቀላል ነው። ነገር ግን እውነተኛ ፍቅር የሚታወቀው ለሌሎች ሰዎች በምንሰጠው ቦታ ነው። ለቤተሰቦቻችንና ለባልንጀሮቻችን ጥንቃቄ ሳናደርግ እግዚአብሔርን እንወደዋለን ማለት ይቻላልን?
2. ዛሬ የተማርከው ምንድነው?

## __ትምህርት፡ 11__

__በብርሃን ትመላለሳለህ__ (1ዮሐ፡5፡1-13)

__መግቢያ፦__ ስለ ፍቅር መማራችንን እንቀጥላለን። እኛ የዘላለም ሕይወት እንዳለን እንድናውቅ ሐዋሪያው ዮሐንስ ይጽፍልናል። ይህን የመጽሐፉን መጨረሻ ክፍል በጥንቃቄ አንብብና በቃሉ ታመን።

1ዮሐ፡5፡1-5 ያለውን አንብብና ‹‹እናውቃለን›› የሚሉ ቃላቶች ላይ የአራት ማዕዘን ምልክት አድርግ፡፡ ደግሞም ‹‹ተወልዷል›› የሚሉ ቃላቶችን አግኝና ከሥር አሥምርባቸው፡፡

ቁ.1 ክርስቶስ ነው ብሎ በኢየሱስ የሚያምን ሁሉ ከእግዚአብሔር ተወልዶአል፣ ወላጁንም የሚወድ ሁሉ ከእርሱ የተወለደውን ደግሞ ይወዳል፡፡
ቁ.2 እግዚአብሔርን ስንወድ ትእዛዛቱንም ስናደርግ የእግዚአብሔርን ልጆች እንድንወድ በዚህ እውቃለን፡፡
ቁ.3 ትእዛዛቱን ልንጠብቅ የእግዚአብሔር ፍቅር ይህ ነውና፤ትእዛዛቱም ከባዶች አይደሉም፡፡
ቁ.4 ከእግዚአብሔር የተወለደ ሁሉ ዓለምን ያሸንፋልና፤ዓለምንም የሚያሸንፈው እምነታችን ነው፡፡
ቁ.5 ኢየሱስም የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆነ ከሚያምን በቀር ዓለምን የሚያሸንፍ ማን ነው?

## <u>የምልከታና የውይይት ሀሳቦች</u>

1. ከእግዚአብሔር የተወለደ ሰው ባሕሪይ ምን ይመስላል?:-
   በቁ፡1______________________________________________________
   በቁ፡2______________________________________________________
   በቁ፡3______________________________________________________
   በቁ፡4 እና 5________________________________________________
2. ዓለምን ያሸነፈ ሕይወት ምን ይመስላል? አንተስ ዓለምን አሸንፈሃል? ወይስ ዓለም አንተን አሸነፈ?

1ዮሐ፡5፡6-13 አንብብ፡፡ በዚህ ክፍል ውስጥ የኢየሱስን ስም የሚጠቅሱ ቃላቶችን ከሥር አስምርባቸው፡፡ እንዲሁም ‹መመስከር› ወይም ‹ምስክርነት› የሚሉ ቃላቶችንም ተመልከት፡፡

ቁ.6 በውሃና በደም የመጣ ይህ ነው እርሱም ኢየሱስ ክርስቶስ በውሃና በደሙ እንጂ በውሃው ብቻ አይደለም፡፡
ቁ.7 መንፈስም እውነት ነውና የሚመሰክረው መንፈስ ነው፡፡
ቁ.8 የሚመሰክሩት መንፈሱና ውሃው ደሙም ሦስት ናቸውና፤ ሦስቱም በአንድ ይስማማሉ፡፡
ቁ.9 የሰውን ምስክር ብንቀበል የእግዚአብሔር ምስክር ከእርሱ ይልቅ ይበልጣል፤ ስለ ልጁ የመሰከረው የእግዚአብሔር ምስክር ይህ ነውና፡፡
ቁ.10 በእግዚአብሔር ልጅ የሚያምን በነፍሱ ምስክር አለው፤ በእግዚአብሔር የማያምን እግዚአብሔር ስለ ልጁ የመሰከረውን ምስክር ስላላመነ ሐሰተኛ አድርጎታል፡፡
ቁ.11 እግዚአብሔርም የዘላለምን ሕይወት እንደሰጠን ይህም ሕይወት በልጁ እንዳለ ምስክሩ ይህ ነው፡፡
ቁ.12 ልጁ ያለው ሕይወት አለው፤የእግዚአብሔር ልጅ የሌለው ሕይወት የለውም፡፡
ቁ.13 የዘላለም ሕይውት እንዳላችሁ ታውቁ ዘንድ በእግዚአብሔር ልጅ ስም ለምታምኑ ይህን ጽፌላችኋለሁ፡፡

**የትርጉምና የውይይት ጥያቄዎች**

1. ‹‹መመስከር›› እና ‹‹ምስክርነት›› ማለት ምን ማለት ነው የሚመሰክር ማነው ቁ.8
2. የሚመሰክሩ ሰዎች ስለ ማን ነው የሚሰክሩት? በዚህ ጊዜ አንዳንድ ሰዎች ኢየሱስ መንፈስ ብቻ እንደሆነ ያምኑ ነበር፡፡ ሌሎች ደግሞ ኢየሱስ ፍጹም ሰው እንደሆነ አያምኑም ነበር፡፡ የሶስቱ ምስክርነት ምን ይመስልሃል?
3. እግዚአብሔር አብ ስለ ኢየሱስ የመሰከረው መቼ ነበር? ቁ፡9 እና 10
4. በቁ፡11 ላይ ያለው ምስክርነት ምንድነው?
5. እነዚህ ለመረዳት የሚያስቸግሩ ክፍሎች ናቸው ይሁን እንጂ የክፍሎቹን እውነት በግልጽ ማወቅ እንችላለን፡፡

ከዚህ በታች ያሉትን ባዶ ቦታዎችን ሙላ፡-

ሀ. በእግዚአብሔር ልጅ የሚያምን ሁሉ በነፍሱ-------------------- አለው፡፡ (ቁ፡10)
ለ. በእግዚአብሔር የሚያምን የዘላለም---------------------- አለው፡፡
ሐ. ----------ያለው -------------- አለው፡፡ (ቁ፡12)

6. አንተ እንድታውቅ ሐዋሪያው ዮሐንስ የሚፈልገው ምንድው?

**ትርጉም**

1. ለአማኞች የዘላለም ሕይወት የሚጀምረው መቼ ነው? በልጁ ስታምኑ ነው ወይስ ከሞት በኂላ? ቁ፡12 እና 13 በጥንቃቄ አንብብ፡፡

**ከሕይወት ጋር ማዛመድ**

አንዳንድ ሰዎች የዘላለም ሕይወት አለን ብለው ተስፋ ያደርጋሉ፡፡ ነገር ግን በዚህ እርግጠኛ እንድንሆን ዮሐንስ ይፈልጋል፡፡ የደህንነታችን መሠረቱ እግዚአብሔር የሰጠን ተስፋ ቃልና ልጁ ነው፡፡ በእግዚአብሔር እውነት የምታምን ከሆነ የዘላለም ሕይወት አለህ ማለት ነው፡፡ ነገር ግን ሁሌ በፍርሃትና በጥርጣሬ የምትኖር ከሆነ ‹‹በእውነት ጌታ ኢየሱስን የሕይወቴ መሪና ጌታ አድርጌ ተቀብያለሁ?›› ‹‹ኢየሱስ በመስቀሉ በሠራው ሥራ አምናለሁ?>> <<ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጁ ፍጹም ሰውና ፍጹም ሰው እንደሆነ አምናለሁ? ብለህ ራስህን መጠየቅ አለብህ፡፡
ይህንን ሁሉ የምታምን ከሆነ በእውነት የእግዚአብሔር ልጅ ነህ፤የዘላለምም ሕይወት አግኝተሃል፡፡

## ትምህርት 12

**በብርሃን ትመላለሳለህ? (1ዮሐ፡5፡13-21)**

**ድምጽህን ከፍ አድርገህ መግቢያውን አንብብ፡፡** በእግዚአብሔር ልጅ የምናምን ከሆነ የዘላለም ሕይወት እንዳለን ባለፈው ሳምንት ተምረን ነበር፡፡ ይህ እጅግ በጣም አስደናቂ ዜና ነው፡፡ ሐዋሪያው ዮሐንስ መልእክቱን ሲጨርስ እኛ ማወቅ የሚገባንን ነገር በማጠቃለያው ትምህርቱ ይደግማል፡፡ ቁ፡16 እና 17 አንነካም፡፡ ምክንያቱም ብዙ ጊዜ ሳናጠናቸው እነዚህን ቁጥሮች መተርጎም ይከብዳል፡፡ ስለዚህ እባካችሁ እነዚህን ሁለት ቁጥሮች እያነበባችሁና እየተወያያችሁ ጊዜ አታጥፉ፡፡ ሐዋሪያው ዮሐንስ ደጋግሞ ሊያስተላልፍ የፈለገውን መልእክት እንሰማለን፡፡ ለምሳሌ አንድ ሰው አንድን መልእክት ደጋግሞ የሚናገር ከሆነ ይህ መልእክት በጣም አስፈላጊ ነው ማለት ነው፡፡

## <u>የምልከታና የውይይት ሀሳቦች</u>

1ዮሐ፡5፡13-15 እና 18-21 ያለውን ክፍል አንብብና ‹‹**እናውቃለን**›› የሚለውን ቃል ከሥሩ አስምርበት፡፡

ቁ.13 የዘላለም ሕይወት እንዳላችሁ ታውቁ ዘንድ በእግዚአብሔር ልጅ ስም ለምታምኑ ይህን ጽፌላችኂለሁ፡፡
ቁ.14 በእርሱ ዘንድ ያለን ድፍረት ይህ ነው፤ እንደ ፈዋዱ አንዳች ብንለምን ይሰማናል፡፡
ቁ.15. የምንለምነውንም ሁሉ እንዲሰማልን ብናውቅ ከእርሱ የለመንነውን ልመና እንደ ተቀበል እናውቃለን፡፡

ቁ18. ከእግዚአብሔር የተወለደ ሁሉ ሐጢአትን እንዳያደርግ ነገር ግን ከእግዚአብሔር የተወለደ ራሱን እንዲጠብቅ ክፉውም እንዳይነካው እናውቃለን፡፡
ቁ.19 ከእግዚአብሔር እንደ ሆንን ዓለምም በሞላው በክፉው እንደተያዘ እናውቃለን፡፡
ቁ.20 የእግዚአብሔርም ልጅ እንደመጣ እውነተኛም የሆነውን እናውቅ ዘንድ ልቡናን እንደ ሰጠን እናውቃለን፤ እውነተኛም በሆነው በእርሱ አለን እርሱም ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ እርሱ እውነተኛ አምላክና የዘላለም ሕይወት ነው፡፡
ቁ.21 ልጆች ሆይ ከጣዖታት ራሳችሁን ጠብቁ፡፡

## <u>ትርጉም</u>

1. ከዚህ በታች ያሉትን ክፍሎች ተመልከት፡፡ ከእነዚህ ክፍሎች እኛ ማወቅ የምንችላቸውን ነገሮች በሙሉ ዘርዝር፡፡
   ሀ.ቁ.13
   ለ.ቁ. 15
   ሐ.ቁ.15
   መ. ቁ.18
   ሠ.ቁ.19
   ረ. ቁ.20
2. ቁ.14 ተመልከት፡፡ ስንጸልይ እንዴት መጸለይ አለብን? እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ወይስ እንደራሳችን ፈቃድ? እንዴት በድፍረት መጸለይ እንችላለን?
3. ክርስቲያኖች ሐጢአት ይሠራሉ፡፡ 1ዮሐ፡1፡8-9 እኛ ሐጢአት ስንሠራ ምን እናደርጋለን?

4. በቁ.18 ላይ እግዚአብሔር የሰጠን ተስፋ ምንድነው?
5. በቁ.21 ላይ ሐዋሪያው ዮሐንስ የሚሰጠን ማስጠንቀቂያ ምንድነው?

**ከሕይወት ጋር ማዛመድ**

ሐዋሪያው ዮሐንስ በመልክቱ ስለ ኢየሱስ ማንነት በጣም አስደናቂ የሆነ ስዕል ይሰጠናል፡፡ በኢየሱስ ላይ ያለን እምነት ዕለት ዕለት በምንኖረው ኑሮ ላይ አዎንታዊ ተጽዕኖ ያመጣል፡፡ በእሱ ላይ ያለን እምነት ለደህንነታችን ቁልፍ ነው፡፡ ጣዖትን ማምለክ በኢየሱስ ላይ ያለንን እምነት ይወስድብናል፤ ደግሞም እኛን ከኢየሱስ ለይቶ እርሱ ለእኛ ሲል በቀራኒዮ መስቀል ላይ የከፈለውን ዋጋና ትንሣኤውን እንድንረሳ ያደርገናል፡፡ ስለዚህ ሐዋሪያው ዮሐንስ መልእክቱን ሲያጠቃልል ስለ ጣዖት አስረግጦ ያስጠነቅቀናል፡፡

ከዚህ በታች ያሉትን ጥያቄዎች መልስ፡-

1. ኢየሱስ ክርስቶስ ማነው? ኢየሱስ በሞቱ ለአንተ ያደረገው ምንድነው?
2. የእውነትን ምንነት መወሰን የምትችለው እንዴት ነው? ጆሮህን ለዓለም ሀሳብ ትሰጣለህ? እምነትህ በሰባኪው ላይ ነው ወይስ በእግዚአብሔር ቃል ላይ?
3. ስለ ሕይወት የእግዚአብሔር ቃል ዛሬ ለአንተ የሚነግርህ ምንድነው?
4. ዛሬ በዘላለም ሕይወት ላይ ጥርጣሬ ቢኖርህ ምን ማድረግ ትችላለህ?

## ትምህርት 13

**በብርሃን ትመላለሳለህ? (መዝ፡51)**

**ድምጽህን ከፍ አድርገህ መግቢያውን አንብብ፡፡** በ1ዮሐ፡1፡9 ላይ የእግዚአብሔር ቃል ሲናገር፡- ‹‹በሐጢአታችን ብንናዘዝ ሐጢአታችንን ይቅር ሊለን ከዓመፃም ሁሉ ሊያነጻን የታመነና ጻድቅ ነው›› ይላል፡፡ ይህ በጣም አስፈላጊ ትምህርት ነው፡፡ ዛሬ መዝ፡51ን እናጠናለን፡፡ ይህንን መዝሙር የጻፈው ንጉሡ ዳዊት ሲሆን ሐጢአት በመሥራቱ ከእግዚአብሔር ምህረትን የለመነበት ነው፡፡ ይህ ዳዊት የለመነው ልመና ዛሬ እኛም በሕይወታችን የሐጢአተኝነት ስሜት ስሰማን ከእግዚአብሔር ምሕረትን መለመን እንችላለን፡፡

መዝ፡51 አንብብ፡፡

1. ዳዊት ፀሎቱን እንዴት ይጀምራል? በቁ.3 እሱ ያመነው ምን ነበር? እሱ ለሠራው ሐጢአት የሚሰጠው ምክንያት አለ? ጊዜ ካለ የዳዊትን ኑዛዜና በ1ሳሙ፡15 ላይ ንጉሡ ሳኦል ከሰጠው ምክንያት ጋር አወዳድር፡፡
2. በቁ.17 ላይ ዳዊት ስለ ሠራው ሐጢአት ምን ተሰማው? ይህ ለምን ይጠቅማል? 2ቆሮ፡7፡10 አንብብ፡፡ በፍጹም ልብ ንስሐ መግባትና በመንፈሳዊ ሕይወት አዝኖ ስለ መመለስ ምን እንማራለን?
3. በቁ.1 እና 7-9 መሠረት አንድ ሰው ሐጢአቱን ከተናዘዘ በኋላ ቀጥሎ ማድረግ ያለበት ምንድነው?
4. በቁ.12-15 መሠረት ዳዊት የሚያምነው ምንድነው?

1ዮሐ፡1፡7 እና 9 አንብብ።
እኛ ከሐጢአትና ከበደል የምንነፃው እንዴት ነው?
ሐጢአተኛ ባሕሪያችንን ለማስወገድ ከእኛ የሚጠበቀው ድርሻ ምንድነው?
በዚህ ክፍል የተዘረዘሩት የእግዚአብሔር ባሕሪያት ምንድናቸው? ለምን?
ሐጢአተኝነት ቢሰማህ ምን ማድረግ አለብህ? በምን ፍጥነት ነው ሐጢአትህ ይቅር የሚባልልህ?

ዳዊት ንስሐ ስለገባ ሐጢአቱ ይቅር ተባለለት። ቢሆንም በሐጢአት የተወለደው ልጁ ሞተ። እሱ ያስተዳድር የነበረው መንግሥት ብዙ ችግሮችን አሳልፏል። አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔር በዚህ ዓለም በሐጢአት ምክንያት የሚመጡ ውጤቶች ቀጣይ እንዲሆኑ ያደርጋል። ለምሳሌ ለብዙ ዓመታት አልኮል ጠጥተህ ሊሆን ይችላል። ከዚህ ሁኔታ ንስሐ ስትገባ እግዚአብሔር ይቅር ይልሃል። ነገር ግን በመጠጡ ምክንያት በጤናህ ላይ የመጡ ችግሮች አይቀረፉልህም። ከእግዚአብሔር ጋር የተሻለ ግንኙነት ይኖርሃል፤ነገር ግን በጤና መታወክ ምክንያት ብዙ ዕድሜ ሳትኖር ልትሞት ትችላለህ። ስለዚህ ምን ታስባለህ?

የሚከተሉትን ሀሳቦች ተወያይና ከሕይወትህ ጋር አዛምድ።
አራቱ ደረጃዎች፡-

1. በሙሉ ልባችን ከሐጢአታችን ንስሐ መግባት አለብን።
2. ለሠራነው ሐጢአት መጸጸት አለብን።
3. ከእግዚአብሔር ይቅርታን መለመን አለብን።
4. እግዚአብሔር ስለ ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስ ሲል ሐጢአታችንን ይቅር እንደሚል ማመን አለብን። እግዚአብሔር ከራሱ ጋር ግንኙነት እንድናደርግ ወደ ራሱ ያስጠጋናል።